# የፀረ ድህነት ትግሉ ስኬት

ሚካኤል ተፈሪ 11/20/12

ሀያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ዓለማችን በሣይንስና ቴክኖሎጂ የመጠቀችበት ዘመን ነው። ይህን ተከትሎ በግለሰቦች፣ በማህበራት በድርጅቶችና በመንግሥታት መካከል በተለያዩ መስኮች ግንኙነት ለማድረግ የሚፈጀው ጊዜ ከወራትና ከሣምንታት ወደ ደቂቃዎች ተሸጋግሯል።

ግሎባላይዜሽን ዓለምን በመረጃ ሥርዓት በማስተሳሰር ወደ መንደርነት ቀይሯታል። አገራት ግሎባላይዜሽን ይዚቸው የመጣውን በጎ ጎኖች ለመጠቀም ከሚያደርጉት ጥረት ጎን ለጎን መጥፎ ጎኑ ከጨዋታ ውጪ እንዳያደርጋቸው የተለያዩ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በማውጣት ሕዝባቸውንና አገራቸውን ለመታደግ እንቅስቃሴያቸውን ገፍተውበታል።

የበለፀጉ አገራት በገነቧቸው ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች፣ የሣይንስና ቴክኖሎጂ ማዕከላት፣ የምርምርና ወታደራዊ ተቋማት በመታገዝ እያንዳንዳቸው ካለው የምጣኔ ሀብት ቀውስ ለመውጣት ጥረት እያደረጉ ቢሆንም ይህን ተከትሎ የመጣው የሥራ አጥነት ፈተና ግን ታላላቅ ከተሞቻቸውን በሠላማዊ ሰልፍ ከማናጋት አላስቀረውም።

የአውሮፓና አሜሪካ ምጣኔ ሀብት ማሽቆልቆል ከፈጠረው የሥራ አጥ ማዕበል በተጨማሪ የዋጋ ግሽበቱ መካከለኛ ኑሮ ላይ የሚገኙ ዜጎች ወጪያቸውን በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀንሱ አስገድዷቸዋል። ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች በሙሉ

ኃይላቸው እንዳያመርቱ በመገደባቸው በሺህዎች የሚቆጠሩ ሠራተኞቻቸውን እንዲያሰናብቱ አድርጓቸዋል።

ዓለም አቀፋዊና አገራዊ ሁኔታዎች ሰዎች በመንግሥት ድርጅቶችና በግለሰብ ካምፓኒዎች ላይ ብቻ ጥገና ሆነው በቅጥር የሚኖሩበትን ዕድል ዘግተውታል። ከዚህም በተጨማሪ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መመረቅ በራሱ የሥራ ዋስትና የሚሆንለትን ዕድል አጨልመውታል።

እነዚህንና ሌሎች ዓለም አቀፍ ሁኔታዎች የሚፈጥሩትን ችግር ከሚያቃልሉ መፍትሔዎች መካከል ሰዎች የራሳቸውን ሥራ እንዲፈጥሩ ማስቻልና ይህንን ለማበረታታት ቁርጠ መነሳት ነው።

እንደ የአገራቱ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ሁኔታ ቢለያይም ድህነትና ሥራ አጥነት የሴቶችን የወጣቶች ዋነኛ ችግር ነው። በተለይ ሥራ አጥነት የታዳጊ አገራት ወጣቶች ችግር ከመሆን አልፎ የማህበራዊ ጠንቆች መንስኤ ጭምር ወደ መሆን ተሸጋግሯል።

ኢትዮጵያ ታዳጊ አገር እንደ መሆኗ መጠን ከላይ የዘረዘርኳቸው ችግሮችም ተቋዳሽ ነበረች። ኢህአዴግ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የነበረባቸውን የዘመናት ጭቆና ራስን በራስ የማስተዳደር፣ ቋንቋቸውን እንዲጠቀሙበት ባህላቸውን እንዲያሳድጉ እንዲያስፋፉ ኃይማኖቶች በእኩል እንዲታዩ በህገ መንግሥቱ ምላሽ በመስጠት ነበር ወደዋነኛው ጠላት ፊቱን ያዞረው።

ጠላታችን ድህነት ነው፣ እጅና እግር ይዘን የሚያስብ ጭንቅላት ይዘን በቀላሉ ሊለማ የሚችል መሬት ይዘን ስንዴ እየለመንን መኖር የለብንም በማለት

ነበር በአንድ ወቅት አቶ መለስ ዜናዊ ለወጣቶችና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መልዕክት ያስተላለፉት።

ከዚህ ጎን ለጎን የወጣቶችና የሴቶች የልማት ፓኬጅ በማውጣት ወጣቶችና ሴቶች ተሳታፊ እንዲሆኑ አድርገዋል። ዛሬ ኢትዮጵያውያን ወጣቶችና ሴቶች በመላው አገሪቱ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ውስጥ በመሰማራት ራሳቸውን ከመጥቀም አልፈው ለአገራቸው ምጣኔ ሀብት ዕድገት አስተዋፅኦ እያደረጉ ይገኛሉ።

መንግሥት ለድህነት ቅነሳና ለሥራ ፈጠራ ልዩ ትኩረት በመስጠቱ በከተማና በገጠር በተጨባጭ ልዩነትን ሊፈጥሩ የሚችሉ ተግባራትን እያከናወነ ነው።

በከተሞች ወጣቶችና ሴቶች በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ተደራጅተው ራሳቸውን እንዲለውጡ ልዩ ልዩ ድጋፎችን አድርጓል። ትናንት በየደጃፎቻቸው ላይ ተሰብስበው ወጪ ወራጁን ሲተነኩሉ የነበሩ ወጣቶች በኮብል ስቶን ሥራ ላይ በመሰማራት ከፍተኛ ጥሪት እንዲቋጥሩና ወደ ሌላ የሥራ መስክ በመሸጋገር ራሳቸውን ወደ መካከለኛ ባለሀብትነት እንዲያበቁ አድርጓል።

የጥቃቅንና አነስተኛና፣ የሥራ ፈጠራ ተግባራት በፍላጎት ላይ ብቻ ተመስርተው ውጤታማ እንደማይሆኑ የታወቀ ነው። በመሆኑም መንግሥት፣ የቴክኒክና ሙያ ተቋማትን በከፍተኛ ቁጥር በመክፈት፣ ወጣቶች ክህሎታቸውን፣ ውስጣዊ ዝንባሌያቸውን፣ ተፈጥሯዊ ችሎታቸውንና ልምዶቻቸውን ከዘመናዊ ትምህርት ጋር ለማዋሀድ እንዲያሳድጉ አድርጓል። በዚህ በመበረታታት በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ሴቶችና ወጣቶች በብረታ

ብረት፣ በሽመና፣ በግንባታ፣ በአገልግሎት ዘርፍና በከተማ ግብርና በመሳተፍ ራሳቸውን ከድህነት አውጥተዋል።

መንግሥት በድህነት ላይ የጀመረው ጠንካራ ዘመቻ ውጤታማ እንዲሆን ወጣቶችንና ሴቶችን በጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ እንዲደራጁና ሥራ እንዲፈጥሩ ሲያደርግ ውጤታማ እንዲሆኑ ልዩ ልዩ ፓኬጆችን ቀርፆ ድጋፍ አድርጓል።

ከእነዚህም መካከል ሴቶችና ወጣቶች ወደ ሥራ ለመግባት የሚያስፈልጋቸውን ፋይናንስ በቀላሉ የሚያቀርቡላቸውን የብድር ተቋማት በማቋቋም የቁጠባ ባህላቸውን እንዲያዳብሩ ባለሙያ መድቦ ግንዛቤ እንዲፈጥርላቸውና እንዲደግፋቸው አድርጓል። በዚህም ትልቅ ውጤት ተገኝቶበታል።

ከዚህም በተጨማሪ ለስራ የተበደሩትን ገንዘብ ውጤታማ በሆነ ተግባር ላይ እንዲያውሉ የተጠና የቢዝነስ ፕላን በመስጠትና የመሥሪያ /የማምረቻ/ ቦታ በማቅረብ በቀጥታ ወደ ሥራ ውስጥ እንዲገቡ ደግፏል።

ሌላው የጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ ችግር የነበረውን የገበያ ትስስርና የመረጃ አቅርቦት ለመፍታትም ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመሆን ረዥም ርቀት የሚባል ክንውን ከውኗል።

ሥራ ፈጣሪዎች የሚያመርቱት ምርት ከፈላጊዎች ጋር እንዲገናኝ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ግብዓቶችን፣ የገበያ ፍላጎቶችንና ምጣኔ ሀብታዊ ሁኔታዎችን የተመለከቱ መረጃዎችን እንዲያገኙ፣ ምርቶቻቸውን እንዲያስተዋውቁና እርስ በርስ እንዲደጋገፉ አመቺ ሁኔታዎችን ፈጥሯል።

መንግሥት ዜጎች ከአገራቸው ሀብት እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከቀየሳቸው ፕሮግራሞች አንዱ የከተማው ነዋሪ በቤቶች ልማት ፕሮጀክት አማካይነት ያለበትን የመኖሪያ ቤት እጥረት መቅረፍ ነው።

ይህ ግዙፍ ፕሮጀክት ሲታቀድ ለዘመናት በመኖሪያ ቤት እጥረት የግለሰብ ማዕድ ቤት ውስጥና አልፎ አልፎም በካርቶን በታሸጉ ደሳሳ ጎጆዎች ውስጥ ሲሰቃይ የነበረውን ከተሜ ነፃ ለማውጣት ነው።

ጎን ለጎን በሚሰራው የመሠረተ ልማት ዝርጋታ የተረሱ አካባቢዎች ነፍስ ዘርተው የከተማው ሥራ አጥ በማህበር በመደራጀትም ሆነ በግል በእነዚህ ፕሮጀክቶች ውስጥ በመሳተፍ ተጠቃሚ እንዲሆን ነው።

ዕቅዱ ባለፉት ሰባት ዓመታት ከፍተኛ ውጤት አስመዝግቧል። በቀላል ቁጥር የማይገለፁ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በቀጥታ በቤቶች ልማት

ፕሮጀክቱ ውስጥ በመሳተፍ ገቢያቸውን ከማሳደጋቸውም በላይ የቴክኖሎጂ ሽግግሩ ተዋናይና ተጠቃሚ ለመሆን ችለዋል።

የግንባታው ዘርፍ የሚጠይቀውን የጉልበት ሠራተኛ የብሎኬት፣ የፕሪካስት፣ የበር፣ የመስኮት፣ የማጠናቀቂያ ሥራ ግብዓቶችን በፍጥነትና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ረገድ የጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ ከፍተኛውን ሚና ተጫውቷል።

በርካታ ኢንተርፕራይዞችም ከፕሮጀክቱ ባገኙት ጥቅምና ክህሎት ራሳቸውን ከጥቃቅንና አነስተኛ በማውጣት ወደ መካከለኛ ባለሀብትነት ተሸጋግረዋል። በከተማ የሚገኙ ሴቶችም በጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ በመደራጀት በቤቶች ፕሮጀክት ከጉልበት ሥራ አንስቶ ለቤቶች የሚሆን ግብዓት እስከማቅረብ

ተሳትፈዋል። በአገልግሎት ዘርፍም ለሠራተኞች ምግብ በማቅረብ ጥሪት ቋጥረዋል። ክህሎታቸውንም አሳድገው ወደመካከለኛ ባለሀብትነትም ተቀላቅለዋል።

የጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ ውጤታማ ከሆነባቸው ተግባራት የሽመና ሥራ አንዱ ነው። ለዘመናት ሳይለወጥ በልምድ ብቻ ይሰሩ የነበሩ ባህላዊ አልባሳትን እሴት በመጨመር ዘመናዊነትን አላብሰው ተወዳጅ እንዲሆን አድርገዋል። በዚህም በአገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ገበያ በማቅረብ ራሳቸውንና አገራቸውን ለመጥቀም ችለዋል።

ዛሬ በከተሞች አካባቢ በተፈጠረው ምጣኔ ሀብታዊ መነቃቃት ሥራ አጥቶ ሳይበላ የሚያድር ዜጋ የለም። አገሪቱ በምትከተለው ገበያ መር የኢኮኖሚ ፖሊሲ በመበረታታት የአገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች በከፍተኛ ሁኔታ ወደ ኢንቨስትመንቱ በመግባታቸው በተፈጠረው የሥራ ዕድል ብዙዎች ተጠቃሚ ሆነዋል።

መንግሥት በአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ ላይ ኢንዱስትሪው ከግብርና ዘርፍ የመሪነት ቦታውን እንደሚረከብ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት የኢንዱስትሪ ፖሊሲው ለጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ዘርፍ

የጀመረውን ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴ በማጠናከር ወደተደራጀና በክህሎት ወደሚመራ ኢንተርፕራይዝ ቀይሮ በትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ማብቂያ ላይ ለሚጠበቀው የኢንዱስትሪ የመሪነት ሚና አስኳል እንዲሆኑ ማድረግ የሁሉንም ኢትዮጵያዊ ድጋፍና ርብርብ ይሻል።

አገሪቱ እያስመዘገበችው ባለው ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት ውስጥ ድህነትን ታሪክ አድርጎ ለማስቀረት የተጀመረው ርብርብ በከተሞች አካባቢ ብቻ ተወስኖ የቀረ አይደለም።

አብዛኛው ዜጋ የሚኖርበት የገጠሩ አካባቢም በድህነት ቅነሳውና በሥራ ፈጠራው መስክ ትኩረት ተሰጥቶት በመሰራቱ ለአጠቃላይ ዕድገቱ ግብርናው የላቀ ሚና እንዲጫወት አስችሎታል።

በገጠር የመሬት ፖሊሲው እንደ ከዚህ ቀደሙ ለአባወራው ብቻ ይሰጥ የነበረውን የበላይነት በማስቀረት ሴቶች ከወንዶች እኩል መሬት እንዲያገኙና አልምተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ አድርጓል።

በዚህም የወንድ ጥገኛ የነበረችዋን የገጠር ሴት ነፃ በማውጣት ለራሷም ለቤተሰቧም መከታ እንድትሆን አስችሏታል በእርሻ መሬት እጦት ምክንያት ወደከተሞች ተሰዶ ለልዩ ልዩ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ችግሮች ሲዳረግ የቆየውም የገጠሩ ወጣት አልተረሳም።

ሰፋፊ የእርሻ መሬት ባሉባቸው አካባቢዎች ወጣቱ የእርሻ መሬት እንዲኖረውና እርሶ ተጠቃሚ እንዲሆን ተደርጓል።

ለእርሻ የሚሆን በቂ መሬት በሌለባቸው አካባቢዎች ወጣቱ በግልም ሆነ በማህበር በመደራጀት ሰፋፊ መሬት በማይጠይቁ ትርፋማነታቸው በተጨባጭ በተረጋገጠ የግብርና ተግባራት ላይ እንዲሳተፉ ተደርጓል በዚህም ውጤት ተገኝቶበታል።

የገጠሩ ወጣት ከመንግሥት በሚደረግለት ልዩ ልዩ ድጋፍ በመበረታታት ለአካባቢው የሚመረቱ ምርቶች ላይ እሴት በመጨመር፣ ለከተማው ነዋሪ እያቀረበ ነው። በሚያገኘው ትርፍም የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ከከተማ እየገዛ ለገጠሩ አርሶ አደርና አርብቶ አደር በማቅረብ ተጠቃሚነቱን ያረጋገጠ ነው።

አገሪቱ እያስመዘገበችው ላለው ሁለንተናዊ የምጣኔ ሀብት ዕድገት ግብርና እያበረከተ ያለው ድርሻ የላቀ ነው። ይህንን የመሪነት ሚና አጠናክሮ እንዲቀጥል በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ውስጥ ትልቅ ቦታ ተሰጥቶታል።

ለዚህም ነው በአርብቶ አደሩና አርሶ አደሩ ባህላዊ አስተራረስ ላይ ብቻ ተንጠልጥሎ የነበረውን የግብርና ልማት ለማስቀረት እረፍት የለሽ ትግል እየተደረገ ያለው ።

የግብርናው ዘርፍ በምርምርና ጥናት ላይ በመደገፍ ለልዩ ልዩ የአገሪቱ ሥነ ምህዳር ተስማሚ የሆነ ግብዓቶችንና ቴክኖሎጂዎችን በማቅረብ ይህንኑ የሚጠቀም የተማረ አርሶ አደርና አርብቶ አደር በመፍጠር ባለፉት ሰባት ተከታታይ ዓመታት በዘርፉ በአማካይ 8 ነጥብ 5 በመቶ ዕድገት ለማስመዝገብ ችሏል። ይህም የመንግሥት፣ የግብርና ባለሙያዎች፣ የአርሶ አደሩና የአርብቶ አደሩ ቅንጅታዊ ተግባር ውጤት ነው።

ሴቶችና ወጣቶች በዚህ ውጤት ውስጥ ትልቁን ድርሻ እየተጫወቱ ነው። ሴቷ መንግሥት ባስቀመጠው ትክክለኛ የገጠር መሬት ፖሊሲ ዋነኛ ተጠቃሚ በመሆኗ ከጥገኝነት ወጥታ ጥሪት በመቋጠር ወደሞዴል አርሶ አደርነት ተቀይራለች። የአኗኗር ዘይቤዋን ቀይራለች።

የአብራኳ ክፋዮች የሆኑ ልጆቿን የከብት ጭራ እየተከተሉ ከመሄድ አላቃ የዘመናዊ ትምህርት ተቋዳሽ እንዲሆኑ አብቅታለች።

መንግሥት፣ ድህነት ትልቁ ጠላታችን ነው በማለት በግልፅ ለሕዝቡ ካስታወቀበት ጊዜ አንስቶ ልዩ ልዩ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በማውጣትና ወደተግባር በመቀየር ውጤታማ ተግባራት ማከናወኑን ከላይ ገልጫለሁ።

በከተሞች የጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፉን በማቋቋም የቤቶች ልማት ፕሮጀክት፣ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ፕሮጀክቶችን የመሳሰሉትን በማቀድና ወደተግባር በመለወጥ የከተማው ወጣቶችና ሴቶች ሥራ እንዲፈጥሩና ተደራጅተው በዕድሉ እንዲጠቀሙ በማድረጉ የፀረ ድህነት ትግሉ በአኩሪ ሁኔታ እየተካሄደ ነው።

በገጠር የአገሪቱ ክፍልም ለግብርናው ዘርፍ በተሰጠው ትኩረት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሞዴል አርሶ አደሮችንና አርብቶ አደሮችን በመፍጠር ወጣቱና ሴቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል።

ከዚህ ጎን ለጎን በኋላቀር አስተራረስ፣ ግጦሽ፣ እንዲሁም ለማገዶ፣ ለቤት ግንባታ ለእርሻ ቦታ ማስፋፊያ ተብለው አለአግባብ በተጨፈጨፉ ደኖች ምክንያት የእርሻ መሬታቸው ተራቁቶ ወንዞችና ምንጮች ደርቀው ህዝቡ ከድህነት ወለል በታች በሆነ ኑሮ በሚኖርባቸው አካባቢዎችና አልፎ...አልፎ በድርቅ የሚጠቁ የአገሪቱ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ከችግር ለማውጣት የተለያዩ ፕሮግራሞችን ነድፎ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል።

ሥር የሰደደ የምግብ ዋስትና መታጣት ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ድህነትን በዘላቂነት ለማስወገድ በግለሰብና በማኅበረሰብ ደረጃ ጥሪት ፈጥረው ራሳቸውን እንዲችሉና ከተረጂነት እንዲላቀቁ መንግሥት የተለያየ የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞችን ነድፏል። ከእነዚህ ውስጥ የልማታዊ ሴፍቲኔትና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ሠፈራ ዋነኞቹ ናቸው።

የዓለማችን ዋነኛ ችግር እየሆነ የመጣው የተፈጥሮ ሀብት መራቆትና የአየር መዛባት አገሪቱን በተለያየ ወቅት ጎብኝቷል። በዚህም ክስተት ድርቅና ረሀብ፣ ረሀብና ኢትዮጵያ የአንድ ሣንቲም ሁለት ገፅታ እስኪመስሉ ድረስ የዓለም ሕዝብ መዘባበቻና መጠቋቋሚያ እስከ መሆን ደርሰን ነበር።

ኢህአዴግና የሚመራው መንግሥት ይህን የአገሪቱን ገፅታ ለመቀየር ኅብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ ያከናወነው ውጤታማ ተግባር በቅርብ ዓመታት በምሥራቅ አፍሪካ ድርቅና ረሀብ ተከስቶ የጎረቤት አገራት ሕዝቦች በረሀብ እንደ ቅጠል ሲረግፉ ኢትዮጵያ ውስጥ ግን በተዘረጋው የአደጋ መከላከል ሥርዓት አማካይነት ሕዝቡን ከሞት መታደግ ተችሏል። በዚህም አሰፍስፈው ሲጠብቁ የነበሩ የውጭ የዜና አውታሮችን ለእፍረት መዳረግ ተችሏል።

በተፈጥሮ ሀብት መራቆት ሣቢያ ለጉዳት የተዳረጉና በድርቅ የተጠቁ አርሶ አደሮችንና አርብቶ አደሮችን ከድህነትና ከኋላ ቀርነት ለማላቀቅ ተፋሰስን መሠረት ያደረጉ የተቀናጁ የአካባቢ መልሶ ማልማት ሥራዎችን በመስራት አልፎ...አልፎ ከዝናብ የሚገኘውን ውኃ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም፣ ውኃን በመያዝና በዚህም የመስኖ ልማት እንዲያካሂዱ በማድረግ ምርታማነታቸውን እንዲያሳድጉ ተደርጓል።

በባህላዊ መልክ ሲካሄድ የነበረውን የእንስሳት ሀብት ልማት፣ ቀስ...በቀስ ለማስቀረት የሚያስችል በምርታማነታቸው የታወቁ የእንስሳት ዝርያዎችን በእነዚህ አካባቢ ለሚኖሩ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች በማቅረብ፣ አዳቅሏል።

እንዲሁም የእንስሳት ሀብት ልማትን ከአግሮ ፎረስተሪ (ጥምር ግብርና) ሥራ ጋር በማያያዝ በተጨማሪም ብዙ ውኃ የማይፈልጉና በአጭር ጊዜ የሚደርሱ አትክልትና ፍራፍሬ ዘሮችን በማደል፣ ዘመናዊ ቀፎዎችን በማቅረብ ኅብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆንና ከተረጂነት እንዲላቀቅ ተከታታይነት ያላቸው ሥራዎች ተሰርተዋል።
በዚህም ውጤት ተገኝቶበታል።

የተገኘውን ምርጥ ተሞክሮ በመቀመርም በሙሉ የአገሪቱ ክፍል የሚገኙ አርሶ አደሮች በአንድ ለአምስት አደረጃጀት በመሰባሰብ የአካባቢ ጥበቃና የመልሶ ማልማት ሥራ እንዲሰሩ ግንዛቤን ፈጥሮላቸዋል።

አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ ሥርዓቱ በፈጠረለት ዴሞክራሲ በመጠቀም እርስ በርስ እየተወያየ ቅድመ አደጋ መከላከል ተግባርን ማከናወኑ በራስ የመተማመን አቅሙን ስለጎለበተለት በቀጣይም በዘመናዊ ዘዴ፣ በሚይንስና በጥናት ተደግፈው በመንግሥት በኩል የሚቀርቡለትን የተፈጥሮ አካባቢ ጥበቃ ሥራዎችን አጠናክሮ በመቀጠል ኢትዮጵያ የታወቀችበትንና በአለም አቀፍ ደረጃ በተለያዩ አገራትና ድርጅቶች ልምድ ያካፈለችበትን የአረንጓዴ ኢነርጂ ልማት ፖሊሲን ተግባራዊ ለማድረግ የበኩሉን ሚና ለመጫወት ቃል የገባበት ወቅት ላይ ነን።

በመሬት ጥበት፣ በአፈር መከላትና ለምነት ማጣት፣ በእርጥበት እጥረት፣ የራሳቸውንና የቤተሰባቸውን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ያልቻሉ ዜጎችን በፈቃደኝነት ለም ወደሆኑ የአገሪቱ ክፍሎች በፈቃደኝነት በማስፈር ውጤታማ የሚባል ተግባር ተከናውኗል።

ሠፈራ በተለይ ለሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ለሚገኙ ዜጎች የምትመር ቃላት ናት። ለምን ቢባል የደርግ መንግሥት ለፍትህ፣ ለእኩልነት፣ ለብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ነፃነት የሚታገሉ ኃይላት ፈጣን ጉዞ ለመግታት የሚቻለው በአካባቢው ለእነዚህ ወገኖች ድጋፍ የሚሰጡ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ከአካባቢው ማራቅ ብቸኛው አማራጭ ነው ብሎ በማመኑ ነው።

ከዚህ በመነሳት ነበር አገር አማን ነው ብሎ ለገበያ ወደ ከተማ የወጣውን ሰው ሁሉ ያታ፣ ዕድሜ፣ ቤተሰብ ሳይለይ አፍሶ ባላወቁትና ባልተዘጋጁበት ሁኔታ ለበረሃ የዳረጋቸው። ቤተሰብ ከቤተሰብ ልጅ ከወላጅ፣ ባል ከሚስት ተለያይተው ለሥቃይ የተጣሉበት ዘመን።

ቅድመ ዝግጅት ያልነበረው፣ ኅብረተሰቡን ያላሳተፈ በፈቃደኝነት ላይ ያልተመሰረተ ነበርና ውጤታማ ሳይሆን የብዙ ዜጎችን ህይወት ቀጥፎ ተጠናቀቀ፣ መንግሥትም የኢትዮጵያ ሕዝብም የዓለም ሕዝብም ይህን ታሪክ በሚገባ ያውቁታል።

በዓይነቱ ልዩ የሆነውና ሁሉንም የአገሪቱን ክፍሎች የነካካው አዲሱ ሰፈራ ግን የተለየ ነው። ዓላማው የሰፋሪዎችን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥና ድህነትን ታሪክ አድርጎ ማስቀረት ነው።

አተገባበሩ ግልፅና ግልጽ ነው ከቅድመ ዝግጅት ይጀምራል። ውይይቱ፣ ሰፋሪውንና የሚሰፍሩበት አካባቢ ያለውን ኅብረተሰብ ያካትታል። መተማመንን፣ መግባባትን፣ ለአንድ ዓላማ አብሮ መሰለፍን ይጠይቃል። መሬት ወሣኝ የተፈጥሮ ሀብት ነው እንክብካቤን ይሻል የባለቤትነት መንፈስን ይጠይቃል።

አካባቢያቸውን እትብታቸው የተቀበረበትን ቀዬ ለቀው ወደሌላው የአገራቸው ክፍል ወደማያውቁት አካባቢ እንዲሰፍሩ ሲደረግ ምክንያታዊነትን ይጠይቃል። ተጨባጩን ኑሮአቸውንና በሰፈራ የሚያገኙትን ለውጥ በሰከነ አኳኋን ማብራራትና ማሳመን የግድ ይላል።

በዚህ ሒደት ነው የመጀመሪያዎቹ 228,343 ቤተሰቦች ወይም 1 ነጥብ 4 ሚሊዮን ሕዝብ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በትግራይና በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦች ክልል ውስጥ በሚገኙ 72 ወረዳዎች ውስጥ በተቋቋሙ የሠፈራ ጣቢያዎች ውስጥ ከ1995 እስከ 2003 ዓ.ም ድረስ በፈቃደኝነት በመስፈር 98 በመቶ ያህሉ በምግብ ራሳቸውን በመቻል ጥሪት ወደመቋጠር እንዲሸጋገሩ የተደረገው።

ከላይ እንደገለፅኩት ሠፈራው የተከናወነው በሁለቱም በኩል ስምምነት ላይ ተደርሶ ነው። ለሠፈራ በተመረጡ አካባቢዎች የሚኖረው ሕዝብ ወደፊት የመሬት ጥበት፣ የተፈጥሮ ሀብት መራቆት፣ የመሳሰሉት ሊገጥመኝ ይችላል በሚል ሥጋት ችግር እንዳይፈጥርና ሠፋሪዎቹን ለመደገፍና በማቋቋም በኩል የራሱን ሚና ከመጫወት እንዳያፈገፍግ በግልፅ ዓላማውን እንዲገነዘብ ተደርጓል።

ከዚህ በተጨማሪ ከሠፈራው ጋር ተያይዞ አካባቢው በመሠረተ ልማት ዝርጋታ፣ በትምህርት፣ በጤና ተቋማት መከፈት ሊያገኘው የሚችለው ዕድል በምጣኔ ሀብታዊ

እንቅስቃሴው ዕድገት ምክንያት ወደአካባቢያቸው የሚስበውን የንግድ ተቋም እንዲሁም በሕዝቦች መካከል በሚፈጠረው ባህላዊ ትስስር የሚከሰቱ መልካም ልምዶችን የራስ ከማድረግ አኳያ ያለውን በጎ ገፅታ፣ የአካባቢያቸውን ተፈጥሮ በጋራ የመጠበቅና የመንከባከብ ኃላፊነት ሁሉ ተወያይተውና ተስማምተው በመሆኑ ለውጤቱ መገኘት ትልቁን ድርሻ ተጫውቷል።

ዜጎች በፈቃደኝነት የሰፈሩባቸው አካባቢዎች ለም መሬትና አስተማማኝ እርጥበት በሚገኝባቸው አካባቢዎች ከመሆናቸው ባሻገር መንግሥት ሠፋሪዎቹ በምግብ ራሳቸውን እንዲችሉና አደጋን የመቋቋም አቅማቸውን እንዲያሳድጉ ካሉበት ቦታ  እስከሚሰፍሩበት ቦታ ያለውን የትራንስፖርት ወጪ ሸፍኗል።

ከዚህም በተጨማሪ የቤት ውስጥ ቁሳቁስ፣ የሌሊት ልብስ የስምንት ወር ቀለብ ከነማጣፈጫው፣ ወደ ተግባር ውስጥ ገብተው ከተረጂነት በፍጥነት እንዲላቀቁ አነስተኛ የእርሻ መሣሪያዎች፣ የእርሻ በሬ፣ ሁለት ሄክታር የእርሻ መሬትና እንደአካባቢው ሁኔታ ከ500 እስከ 1000 ካሬ ሜትር ለመኖሪያ ቤት መሥሪያ የሚሆን ቦታ በመስጠት ድጋፉን ገልጿል።

ሠፈራው በተካሄደባቸው አካባቢዎች አስፈላጊው የማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ተቋማት ማለትም የጤና፣ የትምህርት ተቋማትን፣ የንፁህ የመጠጥ ውኃ፣ የወፍጮና የመጋዘን አገልግሎት እንዲሟላላቸው አድርጓል።

በዚህም በመበረታታት ሠፋሪዎች ያላቸውን ጉልበት ካገኙት ለም መሬት ጋር በማቀናጀት ለምግብነት ከሚውሉ ሰብሎች በተጨማሪ ከፍተኛ ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ ያላቸውንና ለውጭ ምንዛሪ ግኝት የሚጠቅሙ ሰብሎችን በማምረት የምግብ ዋስትናቸውን ከማረጋገጣቸው በላይ ጥሪት በመቋጠርና ካፒታል በመፍጠር ወደ ባለሀብትነት የተሸጋገሩ ሠፋሪዎችን በአጭር ጊዜ ለመፍጠር ተችሏል።

ለሠፈራው መሳካት በቅድመ ሠፈራና በድህረ ሠፈራ የተከናወኑ ተግባራትና ይህንኑ ለማስፈፀም በቁርጠኝነት የተሰለፉ የመንግሥት አካላትና፣ የሕዝብ ተወካዮች የግብርና ባለሙያዎች በሙሉ እምነት ቀያቸውን ለቀው የሠፈሩ ዜጎችና በእንግዳ ተቀባይነታቸው አንቱ የተባሉ ሠፈራው የተከናወነበት አካባቢ የሚኖሩ ዜጎች ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ።

መንግሥት ድህነትን ታሪክ አድርጎ ለማስቀረት በገጠሩ የአገሪቱ ክፍል ያቀዳቸው ተግባራት ውጤታማ ሆነዋል።

የተፈጥሮ ሀብት ሥራዎችን፣ የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን የማህበራዊ ተቋማት የግንባታ ተግባራትን በማከናወን በሚገኝ የምግብ እና የገንዘብ ክፍያዎች በመጠቀም ጊዜያዊ የምግብ ፍላጎታቸውን እያሟሉ ጎን ለጎን የሥራ ባህላቸውን እንዲያዳብሩ የተቀየሰው ልማታዊ የሴፍቲኔት ፕሮግራም ተራቁተው የነበሩ ተራሮች እንዲያገግሙ በዛፎች እንዲሸፈኑና ነጥፈው የነበሩ ምንጮች እንዲፈሱ በማድረግ የሕዝቡን ተስፋ እንዲለመልም አድርጓል።

በጎርፍ ምክንያት ለም አፈራቸውን ያጡ የነበሩ እርሻዎች እንዲጠበቁ እድል ከፍቶላቸዋል። ከዚህ ቀደም የማይታወቁ የግብርና ዘርፍ ሥራዎችም በሰፊው እንዲተገበሩና ለአርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ አማራጭ የገቢ ማግኛ ዘዴ እንዲሆኑ ተደርጓል። በዚህ ሂደት የፀረ ድህነት ትግሉም በስኬት እንደሚደመደም ይታመናል።